

## በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣

## ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

# እ.ኤ.አ ከኦክቶበር1 እስከ ከኖቬምበር 30/2025 የነበረው

# የአየር ጠባይ ግምገማ እና

# በቀሪዎቹ ሁለት የበጋ ወራት የሚኖረው የአየር ጠባይ

# አዝማሚያ እና ምክረ ሃሳብ

ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

# በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣

# ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

## እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ ኖቬምበር 30/2025 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማና በቀሪዎቹ የበጋ ወራት የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ

## አጠቃላይ

ለዘንድሮ የበጋ ወቅት የአየር ጠባይ ትንበያ ከመስጠቱ አስቀድሞ በትሮፒካል ፓስፊክ ውቅያኖስ መካከለኛውና ምሥራቃዊ ክፍል ላይ ቀደም ባሉት ወራት የነበረውና በመጪዉ የበጋ ወቅት የሚኖረው የባህር ወለል ሙቀት ሂደት ላይ ሳይንሳዊ ትንታኔና ጥናት ተደርጓል፡ ፡በበጋ ወራት የምስራቅና የመካከለኛዉ ፓስፊክ ዉቅያኖስ የላይኛዉ የዉሃ አካላት ከመደበኛው በታች መቀዝቀዝ (ENSO La Nina) ክስተት ተጽዕኖ ሥር ሆኖ እንደሚቀጥል በተጨማሪም የህንድ ዉቅያኖስ ከመደበኛው ጋር የተቀራረበ መሞቅ ጋር ተያይዞ የዘንድሮ የበጋው ወቅት (Neutral IOD) ስር ሊሆን እንደሚችል ተመላክቷል፡፡ በተጨማሪም በአትላንቲክ ውቅያኖስ ሰሜናዊ ክፍል እንዲሁም በሜዲትራኒያን ባህር ላይ መደበኛና ከመደበኛው በላይ የባህር ወለል መሞቅ እንደሚኖር ተጠቁሟል። ከዚህ ጋር ተያይዞ በመጪው በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የቦረናና ጉጂ ዞኖች፣ ሲዳማ እና ደቡብ ኢትዮጵያ መደበኛ ዝናብ፣ የሶማሌ ክልል ደቡባዊ ክፍል ድግሞ ከመደበኛ በታች የሆነ የዝናብ መጠንና ስርጭት እንደሚኖራቸዉ ትንበያ ተሰጥቷል፡፡ እንዲሁም የምዕራብና ደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ከመደበኛ በላይ ዝናብ እንደሚያገኙ፣ በተጨማሪም እየተስተዋሉ ከሚገኙት የአየር ሁኔታ ክስተቶች ላይ በመነሳት በሰሜን፣ በመካከለኛው፣ በምስራቅና በሰሜን ምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ እንደሚኖር በትንበያዉ ተመላክቶ ነበር፡

በተጨማሪም በሰሜን ምስራቅ፣ በምስራቅና በደቡብ ከፍተኛ ቦታዎች ላይ የቀኑ ዝቅተኛ የሙቀት መጠን ከ 5 ዲግሪ ሴልሽየስ በታች እንደሚሆን የሚጠበቅ ሲሆን፣ ከዚሁ ጋር ተያይዞ የውርጭ ክስተት በሚዘወተርባቸው በሰሜን ምስራቅ በመካከለኛው እና በምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ውርጭ የመከሰት ዕድሉ ከፍተኛ እንደሚሆን የትንበያ ተስቶ ነበር፡፡


በዚህ ጽሁፍ ውስጥ ባለፉት ሁለት የበጋ ወራት የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማና በቀሪዎቹ ወራት ሊኖር የሚችለው የአየር ጠባይ አዝማሚያ እንዲሁም በግብርናው፣ በዉሃ ሴክተሮች እና በጤና ላይ አሳድሮ የነበረው የዳሰሳ እንዲሁም ወደፊትም ሊፈጥር በሚችለው ተፅእኖ ላይ ጽሁፍ ቀርቧል።

## 1.1 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ ኖቬምበር 30/2025 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማ

ባለፉት ሁለት የበጋ ወራት ወደ ሀገራችን ሲገባ የነበረዉ ዕርጥበት አዘል አየር በተለይም በኦክቶበር ወር ላይ ከመጠናከሩ ጋር ተያይዞ ለበጋ ዝናብ መፈጠር ምቹ የሆኑ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ከቀን ወደ ቀን እየተስፋፉ ከመምጣታቸዉ ጋር ተያይዞ፤ በተለይም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ በሁኑት የደቡብ አጋማሽ የሀገሪቱ ስፍራዎች ላይ እንዲሁም በክረምት ወቅት ዝናብ ሲያገኙ የነበሩት የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ የተሻላ ገጽታ ነበራቸዉ፡፡ በመሆኑም፤ በዚህ ወቅት በመደበኛ ሁኔታ ዝናብ የሚያገኙት የደቡብ ኦሮሚያ ዞኖች፣ የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ደቡባዊ ዞኖች፣ የደቡብ እና የደቡብ ምስራቅ ሶማሊ ዞኖች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ የተመዘገበ ሲሆን፤ አልፎ አልፎ ጠንከር ያለ የደመና ክምችት ተስተውሎባቸዋል። እንዲሁም ለዝናብ መኖር አመቺ ሁኔታ የሚፈጥሩ የአየር ሁኔታ ክስተቶች መጠናከር በማሣየታቸው ምክንያት በምዕራብ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከነበራቸው የደመና ሽፋን በመጠንም ሆነ በስርጭት የተሻለ ዝናብ የነበራቸው ሲሆን፤ በተለይም በዚህ ወቅት በመደበኛ ሁኔታ ደረቃማ የአየር ሁኔታ የሚስተዋልባቸዉ የሰሜን ምዕራብ፣ ምዕራብ እና ሰሜን የሀገሪቱ አከባቢዎች በአንዳንድ ቦታዎቻቸዉ ላይ አልፎ አልፎ በነበሩት ቀናት ወቅቱን ያልጠበቀ አነስተኛ መጠን ያለዉ ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ በተጨማሪም አልፎ አልፎ ከነበረዉ የደመና ክምችት በጥቂት ስፍራዎች ላይ ቀላል መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቧል፡፡


በአጠቃላይ በኦክቶብር እና በኖቬምበር ወር ውስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው ጣቢዎች ለመጥቀስም ያህል አዲስ አበባ ቦሌ 37፣ በህር ዳር 35.2፣ 46.2፣ 33.8፣ ጎሬ 55.6፣ 31.9፣ ጅማ 32.4፣ ነገሌ 34.5፣ ነቀምት 76፣ አቦቦ 37.4፣ አዴት 36፣ አማን 54.6፣ አርጆ 41.4፣ አሶሳ 34.7፣ 54.2፣ አየሁ 31.8፣ ቦሬ 36፣ 46.2፣ ቡለን 38.4፣ 38.2፣ 38.2፣ 32.2፣ ቡሬ 60.5፣ 41፣ 70.7፣ 31.5፣ ቻግኒ 30.5፣ ጨዋቃ 30፣ ዲላ 35፣ ዶሎመና 30.3፣ 30.4፣ ኢጃጂ 47.7፣ ፉኙዶ 32፣ ጋምቤላ 51.8፣ ጊዳ አያና 39.2፣ ቡሌ ሆራ 40፣ ጅንካ 37.7፣ ካቺሴ 35.5፣ ቀብሪ ደሃር 35.9፣ ላሬ 31.4፣ ሊሙገነት 57.5፣ 42.7፣ 39.4፣ ማጂ 31፣ 50.8፣ ማንኩሽ 31፣ ማሻ 90.2፣ 30.4፣ 30.6፣ ምዕራብ አባያ 37፣ ነጆ 34.4፣ 34.5፣ ፓዌ 38.5፣ ሰዉላ 31.2፣ 32.8፣ ሻምቡ 35.8፣ ሽሬ 34.8፣ ቴፒ 54.8፣ ተርጫ 43፣ ያቤሎ 66.4፣ አቦሞሪንጋ 34.6፣ 43.2፣ 52፣ 33.6፣ አጋሮ 33፣ አታንጎ 49፣ 46.5፣ ቢላምቢሎ 33፣ 44.6፣ 36፣ ቦርቃ 42.3፣ መንደር 7 35.7፣ ደበረ ሲና 54.2 ዲመካ 36.7፣ እርምጭ 31.3፣ ጉበይሬ 75.6፣ ጉብቴ 34.7፣ 33.9፣ 33.6፣ 37.3፣ 49.4፣ 59.8፣ 37.8፣ 47.8፣ 48.6፣ 32.8፣ ሃሮ 30.2፣ ሃንቲ 31.4፣

ቅዳሜ ገበያ 48.8፣ 37.6፣ 58.6፣ 59.8፣ 48.6፣ 56.7፣ 46.3፣ 48.6፣ 36.8፣ ኮበን 33፣ 37.5፣ 35.5፣ 33፣ ሙጊ 37.7፣ 47.5፣ ኦንጋ 43.3፣ 42.6፣ ተርኮዲ 36.8፣ ትንሹ መጢ 31.3፣ 36.8፣ መንደር 11 46፣ 53.5፣ 96፣ ያንፋ 40.3፣ 30.3፣ 37.8፣ 30.3፣ 37.8፣ 38.4፣ 48.2፣ 30.3፣ 43.5 እንዲሁም ያዮ 42.5 በሚ.ሜ ይገኙበታል፡፡ በአጠቃላይ ባለፉት ሁለት የበጋ ወራት በስልሳ አራት(64) የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሠዓት ዉስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ የሆነ ከባድ መጠን ያለዉ የዝናብ መጠን ነበራቸዉ ፡፡ በተጨማሪም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታች በሁኑት የደቡብ አጋማሽ የሀገሪቱ አከባቢዎች እንዲሁም በአንዳንድ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑ የምዕራብና የደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ 50.8- 96 ሚ.ሜ የሚደርስ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቧል (ምስል 1) ፡፡




ምስል፡1 ከኦክቶበር 1 እስከ ኖቬምበር 30/2025 በ24 ሰዓት ውስጥ ከ50 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው

በሌላ በኩል ባለፉት ሁለት የበጋ ወራት የሌሊትና የማለዳው ቅዝቃዜ እምብዛም ያልተጠናከረ ቢሆንም፤ ከኖቬምበር አጋማሽ በኃላ ከሳይቤሪያ ከፍተኛ የአየር ግፊት ላይ በመነሳት ወደ ሀገራችን የሚነፍሰው ደረቅ እና ቀዝቃዛ አየር ከመጠናከሩ ጋር በተያያዘም የበጋው ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ በተለይም በሰሜን፣ ምስራቅ፣ መከከለኛዉና ደቡብ ደጋማ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የለሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ ከአምስት (5) ዲግሪ ሴልሺየስ በታች በታች ሆኖ ተመዝግቧል (ምስል 2) ፡፡




ምስል 2፡ ከኦክቶበር 1 እስከ ኖቬምበር 30/2025 በ24 ሰዓት ውስጥ ከአምስት (5) ዲግሪ ሴልሺየስ በታች

Ethiopian Meteorology Institute


ባለፈዉ የበጋ ወቅት አጋማሽ የዘነበው የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም በተለይም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት ከኦሮሚያ ክልል ጉጂና ምዕራብ ጉጂ፣ ቦረናና ምስራቅ ቦረና፣ ባሌና ምስራቅ ባሌ፣ አርሲና ምዕራብ አርሲ፤ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ወላይታ፣ ጋሞ፣ ጌዲኦ፣ ደቡብ ኦሞ፣ ቡርጂ፣ ኮንሶ፣ አሊ እና ባስኬቶ ዞኖች፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች፣ ከሶማሌ ክልል የዳዋ፣ የሊበን፣ አፍዴር፣ የሸበል፣ የነጎብ፣ የቆራሂ የዶሎ፣ የኤረር እና የጃረር ዞኖች ከ31-200 ሚ.ሜ የሚደርስ ከ9-24 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ፡፡

በተመሳሳይ ቀደም ብሎ የክረምት ወቅት ዝናብ ሰያገኙ የነበሩት ከኦሮሚያ ክልል የቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ ዞኖች፤ ከጋምቤላ ክልል አኝዋክ፣ መዥንግ፣ የኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ፤ ከቤንሻንጉል ጉምዝ ካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ዞኖች፣ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ኮንታ፣ ዳዉሮ፣ ከፋ፣ ሸካ፣ ቤንች ሸኮ ዞኖች ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል የጎፋ፣ የወላይታ እና ጌዲዮ ዞኖች፣ የሲዳማ ክልል ዞኖች ላይ ከ151-700 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ13-44 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2)፡፡


በሌላ በኩል ከአማራ ክልል የሰሜን፣ መከከለኛዉ፣ ምዕራብና ደቡብ ጎንደር፣ የሰሜን፣ የምዕራብና የምስራቅ ጎጃም፣ የአዊ፣ የባህርዳር ዙሪያ ዞኖች፣ ዞኖች፣ ከትግራይ ክልል ጥቂት የምዕራብና ሰሜን ምዕራብ ትግራይ ዞኖች ላይ ከ31-200 ሚ.ሜ የሚደርስ ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ ከ5-12 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2) ፡፡

ባለፉት ሁለት የበጋ ወራት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ ከሆኑት የሀገሪቱ አከባቢዎች ከኦሮሚያ ክልል የቦረና፣ የምስራቅ ቦረና፣ የጉጂ እና ምዕራብ ጉጂ ዞኖች፣ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል የጋሞ፣ ባስኬቶ፣ አሪ፣ ኮንሶ፣ ቡርጂ፣ አሌ፣ ጋርዱላ፣ ኮሬ እና ደቡብ ኦሞ ዞኖች፣ ከሱማሌ ዳዋ፣ ሊበን፣ ቆራሂ ዞኖች ላይ በአብዛኛዉ ከመደበኛ ጋር የተቀራረበ የዝናብ መጠን ሲመዘገብ የአፍዴር፣ ሽበሌ፣ ኖጎብ፣ ጃራር እና ዶሎ ዞኖች ከመደበኛ በተች የዝናብ መጠን ተመዝግቧል (ካርታ 3) ፡፡


Ethiopian Meteorology Institute




ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ ከኖቬምበር 30/2025 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ ከኖቬምበር 30/2025 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት ብዛት





ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ ከኖቬምበር 30/2025 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር


## እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ ኖቬምበር 30/2025 የነበረው የአየር ጠባይ በግብርና ስራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

በመደበኛ ሁኔታ የበጋ ወቅት አጋማሽ ወራት በአመዛኙ ደረቃማ ሁኔታ የሚያመዝንበት ወቅት ሲሆን ከግብርና እንቅስቃሴ አንፃርም የመኸር አብቃይ በሆኑ አካባቢዎች የሰብል ስብሰባና ድኅረ ሰብል ስብሰባ በስፋት የሚካሄድበት እንዲሁም በደቡብና በደቡብ ምሥራቅ አርብቶ አደርና ከፊል አረብቶ አደሩ አከባቢዎች ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውሃ አቅርቦት አመቺ ሁኔታ የሚኖርበት ወቅት ነው። በአንጻሩ የበጋ ወቅት እንደ ዋግ የመሳሰሉ የሰብል በሽታና ተባይ የሚከሰትበት በተጨማሪም በአንዳንድ ደጋማ አካባቢዎች የውርጭ ክስተት በአዝርዕት እድገት ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድረበት ወቅት ነው።

እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 2025 እስከ በኖቨምበር 2025 የበጋ አጋማሽ ወራት ሲታይ በኦክቶበር እና በኖቨምበር የነበራቸው የእርጥበት ሁኔታ ሲገመገም በተለይም የክረምቱ ዝናብ ሰጪ ክስተቶች ቀስ በቀስ ከመዳከሙ ጋር ተያይዞ የእርጥበት ሁኔታው ከሰሜንና ከሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ በመጠንም ሆነ በስርጭት እየቀነሰ በአንጻሩ በምእራብ አጋማሽ እና በመካከለኛዉ የአገሪቱ ክፍሎች ላይ በተወሰነ ደረጃ የቆየበትና በሂደትም የበጋ ዝናብ ተጠቃሚ ወደ ሆኑት ወደ ደቡብና ደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የተስፋፋ እንደነበረ ተስተውሏል፡፡ ይህም ሁኔታ በሰሜንና በሰሜን ምስራቅ አካባቢዎች ለሚገኙ ለደረሱና ተጨማሪ እርጥበት የማያስፈልጋቸው ሰብሎችን ለመሰብሰብ በጎ ጎን ነበረው። በሌላ መልኩ በምዕራብ አጋማሽና በመካከለኛው የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ እርጥበቱ የተሻለ ገፅታ የነበረው መሆኑ በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ይገኙ ለነበሩ ሰብሎችም ሆነ በአካባቢዎቹ ለሚገኙ ቋሚ ተክሎች በጎ ሚና ነበረው፡፡ በአንጻሩ በኖቨምበር ወር በመደበኛ ሁኔታ ደረቃማ የአየር ሁኔታ በሚስተዋልባቸው በተለይም አልፎ አልፎ በሰሜን፣ በሰሜን ምራብና በመእራብ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ሰብል በደረሰባቸው አካባቢዎች የነበረው ወቅቱን ያልጠበቀ እርጥበት በመጠኑም ቢሆን አሉታዊ ተፅእኖ ነበረው። በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የደቡብና የደቡብ ምስራቅ የሀገራችን አካባቢዎች በተለይም በቦረና፣ ጉጂ እና የደቡብ ክልል ደቡባዊ ዞኖች ላይ የተስተዋለው የእርጥበት ሁኔታ ለአርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች ለግጦሽ ሣርና ለመጠጥ ውሀ አቅርቦት ጠቀሜታ ነበረው (ካርታ 4ሀ እና 4ለ) ፡፡





ካርታ 4ሀ፡ በኦክቶበር 2025 ወር የነበረዉ የእርጥበት ሁኔታ





ካርታ4ለ፡በኖቬምበር 2025 ወር የነበረዉ የእርጥበት ሁኔታ

## እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ ኖቬምበር 30/2025 የነበረው የአየር ጠባይ በዉሀዉ ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉት ሁለት ወራት በተለያዩ የሀገሪቱ ተፋሰሶች ላይ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ስንመለከት በተለይም በኦክቶበር ወር በአብዛኛው አባይ፣ ባሮ አኮቦ፣ ኦሞ ጊቤ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ ገናሌ ዳዋ፣ ዋቢ ሸበሌ፣ እንዲሁም በመካከለኛው እና በታችኛው ተከዜ ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እስከ ከፍተኛ የገፀ ምድር ውኃ ፍሰት ነበራቸው፡፡ በተጨማሪም በመካከለኛው ኦሞ ጊቤ፣ በላይኛው ባሮ አኮቦ፣ በመካከለኛው እና ታችኛው አባይ፣ በጥቂት የላይኛው ገናሌ ዳዋ ተፋሰሶች ላይ በጣም ከፍተኛ የገፀ ምድር ውኃ አግኝተዋል፡፡ ሆኖም የበጋ ተጠቃሚ ተፋሰሶች የሆኑት የመካከለኛው እና የታችኛው ኦሞ ጊቤ፣ የታችኛው ስምጥ ሸለቆ፣ በጥቂት ላይኛው ዋቤ ሸበሌ በተጨማሪም ወቅታቸው ባለሆኑ ተፋሰሶች በመካከለኛና ታችኛው አባይ፣ እንዲሁም በጥቂት መካከለኛው ተከዜ ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እስከ ከፍተኛ የገጸ ምድር የውሃ ፍሰት የነበራቸው ሲሆን ይህ ሁኔታ በአብዛኛው ተፋሰሶች ላይ የሚገኙ በሰው ሰራሽ የውሃ መያዣ ግድቦች ከረዥም ጊዜ አማካይ ጋር ሲነፃፀር የተሻለ ውሃ እንዲይዙ ያስቻለ ነበር፡፡ ካርታ ሀ እና ለ የበጋ አጋማሽ ካርታ ( ካርታ 5 ሀ እና ለ)፡፡







ካርታ 5ሀ፡በኦክቶበር 2025 ወር በተፋሰሶች ላይ የነበረው የእርጥበት መጠን

ካርታ 5ለ፡በኖቬምበር 2025 ወር በተፋሰሶች ላይ የነበረው የእርጥበት መጠን

## እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ ኖቬምበር 30/2025 የነበረው የአየር ጠባይ በጤናው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

እ.ኤ.አ ባሳለፍነው የኦክቶበርና የኖቨምበር 2025 ወራቶች ላይ የነበረው የአየር ጠባይ ሁኔታ በሰዎች ጤና ላይ ያሳደረውን ተጽዕኖ ስንመለከት በተለይም በኦክቶበር ወር አብዛኛው የሀገራችን ክፍል ለወባ መራባትና ስርጭት ከፍተኛ አስተዋፅዖ የነበረው ሲሆን ይህም ሁኔታ በጥቂት የምዕራብ አማራ ዞኖች፣ በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል፣ በሁሉም የምዕራብና የደቡብ ኦሮሚያ ዞኖች፣ በአብዛኛው የጋምቤላ ክልል፣ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል፣ የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል፣ የሲዳማ ክልል፣ የመካከለኛው ኢትዮጵያ ክልል እንዲሁም የደቡብ ምዕራብ ሶማሌ ክልል ዞኖች ለወባ ትንኝ መራባትና ስርጭት ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ ምቹ የአየር ጠባይ ነበራቸው (ካርታ 6)።





ካርታ 6፡ የበጋ ሁለት ወራቶች ወር ለወባ ስርጭት ምቹ የሆኑ ቦታዎች




Ethiopian Meteorology Institute

በሌላ በኩል ባሳለፈነው ሁለት የበጋ ወራቶች ላይ የነበረው የሙቀት ተፅዕኖ ስንመለከት በአብዛኛው የሃገሪቱ ክፍሎች ለሰውም ሆነ ለእንስሳት ተስማሚ እንደነበረ የተተነተኑ የጤና ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመለክታሉ። ሆኖም ግን በተወሰኑ የጋምቤላ፣ የአፋር፣ የምዕራብ አማራ ዝቅተኛ ቦታዎች እንዲሁም የደቡብ እና የሰሜን ሱማሌ ዝቅተኛ ቦታዎች ላይ አስጨናቂ የሙቀት ሁኔታ የነበር በመሆኑ በሰዎችም የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴና በእንስሳት ምርትና ምርታማነት እንዲሁም ጤንነት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እንደነበረው መረጃዎች ያሳያሉ (ካርታ 6 ለ እና ሐ)።




ካርታ 6ለ ፡ አጋማሽ የበጋ ወቅት ለሰዎች የነበረው የምቾት ሁኔታ




ካርታ 6 ሐ፡ አጋማሽ የበጋ ወቅት ለእንስሳት የነበረው የምቾት ሁኔታ

Ethiopian Meteorology Institute

# በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣ ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

## ኢ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1/2025 እስከ ጃንዋሪ 31/2026 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ

በመደበኛ ሁኔታ የዲሴምበር እና የጃንዋሪ ወራቶች በአብዛኛው የበጋ ወቅት የአየር ጠባይ ገፅታዎች የሆኑት ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ የሚያመዝኑበት ከመሆኑም በተጨማሪ የሌሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ በተለይም ለውርጭ ተጋላጭ በሆኑ ደጋማ ቦታዎች ላይ የሚያይልበት ጊዜ ነው። በአንፃሩ አነስተኛ መጠን ያለው ዝናብ በደቡብና በደቡብ ምሥራቅ ኢትዮጵያ እንዲሁም ከበልግ ወቅት መቃረብ ጋር ተያይዞም በጥቂት የሰሜን ምሥራቅ ቦታዎች ላይ ዝናብ ይስተዋላል።

በመጪዎቹ ሁለት የበጋ ወራት የትሮፒካል ፓስፊክ ውቅያኖስ አብዛኛው ክፍል የባህር ወለል ቅዝቃዜዉ እየቀነሰ እንደሚገኝ የተተነበየ ሲሆን፣ በቀሪዎቹ ሁለት የበጋ ወራት ኢ.ኤ.አ 2025-26 (ዲሴምበር እና ጃንዋሪ) ከመደበኛው ጋር የተቀራረበ የትሮፒካል ፓስፊክ ውቅያኖስ የባህር ወለል ሙቀት ከታህሳስ ወር በኋላ ቀስ በቀስ ቅዝቃዜዉ ከመደበኛዉ ጋር የተቀራረበ (Enso-Neutral) እንደሚሆን እንዲሁም የህንድ ውቅያኖስ የባህር ወለል ሙቀት ከመደበኛው ጋር የተቀራረበ (Neutral-IOD) እንደሚሆን የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ።

በመሆኑም በቀጣዮቹ ሁለት የበጋ ወራቶች በአብዛኛው የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ የበጋው ደረቅ፣ ጸሀያማውና ነፋሻማው የአየር ሁኔታ እንደሚዘወተርባቸው የትንበያ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ በተለይም በምስራቅ፣ ሰሜን ምስራቅ እና መካከለኛው የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ የቀኑ ዝቅተኛ የሙቀት መጠን ከ 5 ዲግሪ ሴልሽየስ በታች ሊሆን እንደሚችል የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡

በሌላ በኩል ከሚኖረው የደመና ሽፋን ላይ በመነሳት በጥቂት የሰሜን፣ መካከለኛዉ፣ ምዕራብና ደቡብ ጎንደር ዞኖች፣ ባህርዳር ዙሪያ፣ አዊ፣ በምዕራብና ምስራቅ ጎጃም፣ የምዕራብ ኦሮሚያ ክልል ዞኖች፣ አርሲ እና ምዕራብ አርሲ፣ ባሌ እና ምስራቅ ባሌ ዞኖች፣ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል መተከል፣ አሶሳ፣ ካማሺ እና የማኦኮሞ ልዩ ዞን፣ የጋምቤላ ክልል ዞኖች፣ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች በተለይም በዲስምበር ወር ላይ አልፎ አልፎ በሚኖሩት ቀናት ወቅቱን ያልጠበቀ አነስተኛ መጠን ያለዉ ዝናብ ያገኛሉ፡፡ ስለሆነም በሚኖሩት ደረቅ ቀናቶች የደረሱ ሰብሎች መሰብሰብ አስፈላጊ መሆኑን የኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት ይጠቁማል፡፡ በሌላ በኩል ከበልግ ወቅት መቃረብ ጋር ተያይዞም ከጃንዋሪ አጋማሽ በዋለ በጥቂት የሰሜን ምሥራቅ ቦታዎች ላይ አነስትኛ መጠን ያለዉ ዝናብ ይኖራቸዋል።

## በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣ ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

### እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1/2025 እስከ ጃንዋሪ 31/2026 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በግብርና ስራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በመጪዎቹ የዲሴምበር እና የጃንዋሪ ሁለት የበጋ ወራት በአብዛኛው የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የበጋው ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ ስለሚያመዝን በወቅቱ እየተከናወነ ላለው የግብርና እንቅስቃሴ በጎ ጎን ይኖረዋል፡፡ በመሆኑም በመጪዎቹ ወራት በአብዛኛው የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የሚጠበቀው ደረቅ የአየር ሁኔታ የደረሱ ሰብሎች እንዲደርቁ፤ በጊዜ እንዲሰበሰቡና የድህረ ሰብል ስብሰባ ተግባራትን ለማከናወን አመቺ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡ በሌላ በኩል በአንዳንድ ደጋማ በሆኑ የሀገሪቱ ከፍተኛ ቦታዎች ላይ ከቀኑ ዝቅተኛ የሙቀት መጠን የተነሳ በሌሊትና በማለዳ ሊስተዋል የሚችለው ቅዝቃዜና የውርጭ ክስተት በእንሰሳትም ሆነ በመስኖ በመታገዝ ለሚለሙ አትክልቶች፣ የፍራፍሬ ተክሎች እንዲሁም በቋሚ ተክሎች እድገት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ስለሚኖረዉ አስፈላጊውን ቅድመ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል።

በአንፃሩ በዲስምበር ወር ላይ በጥቂት የሰሜን፣ መካከለኛዉ፣ ምዕራብና ደቡብ ጎንደር፣ ባህርዳር ዙሪያ፣ አዊ፣ ምዕራብና ምስራቅ ጎጃም፤ ምዕራብ ኦሮሚያ፣ አርሲ እና ምዕራብ አርሲ፤ ባሌ እና ምስራቅ ባሌ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ካማሺ፣ ማኦኮሞ ልዩ ዞን፤ ጋምቤላ ክልል፣ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች ላይ አልፎ አልፎ በሚኖሩት ቀናት ወቅቱን ያልጠበቀ አነስተኛ መጠን እርጥበት የሚጠበቅ ሲሆን፤ ይህም ሁኔታ የድህረ ሰብል ስብሰባ በሚከናወንባቸዉ አካባቢዎች ጉዳት እንዳያደርስ አስፈላጊውን ጥንቃቄ በማድረግ በሚኖሩት ደረቅ ቀናቶች የደረሱ ሰብሎች እንድሰበስቡ ይመከራል፡፡ በተጨማሪም ከጃንዋሪ ወር አጋማ በኋላ የሚገኘው አነስተኛ መጠን ያለዉ እርጥበት የበልግ ወቅት የእርሻ እንቅስቃሴን ቀድመው ለሚጀምሩት በደቡብ፣ በደቡብ ምዕራብ፣ በምሥራቅ አማራ፣ እንዲሁም በሰሜን ሸዋ አካባቢ ለሚካሄደው ለማሳ ዝግጅት የእርሻ እንቅስቃሴ ምቹ ሁኔታን እንደሚፈጥር ነው፡፡

### እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1/2025 እስከ ጃንዋሪ 31/2026 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት የዲሴምበር እና የጃንዋሪ ሁለት ወራት የሚኖረው የአየር ጠባይ በዉሀዉ ዘርፍ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ስንመለከት በመጀመርያው ዴሴምበር ወር በአብዛኛው የሀገሪቱ ተፋሰሶች ላይ የበጋው ደረቅ እና ከፊል ደረቅ እንደሚሆን የሚጠበቅ ሲሆን በሌላ

በኩል በደቡብ እና ደቡብ ምስራቅ መጠነኛ የገፀ ምድር ውሃ የሚያገኙበት ወቅት ከመሆኑ ጋር ተያይዞ በመካከለኛው እና በታችኛው ኦሞ ጊቤ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ ገናሌ ዳዋ፣ በመካከለኛው ዋቤ ሸበሌ፣ እንዲሁም በላይኛው እና መካከለኛው ባሮ አኮቦ ተፋሰሶች መጠነኛ የገፀ ምድር የውሃ ፍሰት ያገኛሉ፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ የሚገኘው ውሃ በተገቢ ሁኔታ በማሰባሰብ ውሃን ለዘላቂ ጥቅም ክብከነት እና ከብክለት መጠቅ ይመከራል፡፡ የተቀሩት ተፋሰሶች ላይ በአብዛኛው አዋሽ፣ ተከዜ፣ አባይ፣ አፋር ደናክል፣ ኦጋዴን፣ አባይ፣ በላይኛው እና መካከለኛው ስምጥ ሸለቆ እና ኦሞ ጊቤ ደረቅ ሆነው እንደሚቆዩ ይጠበቃል፡፡

## እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1/2025 እስከ ጃንዋሪ 31/2026 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በጤናው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በመጪዎቹ የዲሴምበርና የጃንዋሪ ሁለት የበጋ ወራቶች ላይ የሚኖረው የአየር ሁኔታ በጤና ላይ ሊያሳድር የሚችለውን የተጽዕኖ ትንበያ ስንመለከት፡ በቀጣይ ሁለት ወራቶች ምንም አይነት ምቹ የሆነ የአየር ሁኔታ ለወባ መፈጠረና ስርጭት የሚስተዋል ባይሆንም ነገር ግን ባሳለፍናቸው ሁለት የበጋ ወራቶች ላይ የነበረው ምቹ የአየር ሁኔታ ለወባ እና ለትንኝ ወለድ በሽታዎች ስርጭት ምቹ የሚሆንበት ሁኔታ የሚፈጠርበት ወራቶች ናቸው። ስለሆነም በኦክቶበርና ኖቬምበር ወራቶች ላይ የነበረውን ምቹ ሁኔታ በሰዎች ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እንዳያመጣ ማህበረሰቡ እና የሚመለከተው አካል ለወባ ተጋላጭ የሆኑ ቦታዎችን ማፅዳትና መከላከል ያስፈልጋል።

በሌላ በኩል በመጪዎቹ የዲሴምበርና የጃንዋሪ ወራቶች ላይ የሚኖረውን የአየር ጠባይ ሁኔታ በሰው ልጅ የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ እና በእሰሳት ተዋጽኦ ላይ ሊያሳድር የሚችለውን ተጽዕኖ ስንመለከት፣ በሀገራችን የደቡብ፣ የሰሜን እንዲሁም የመካከለኛው ከፍተኛ ቦታዎች ላይ የጠዋቱና የማታው የቅዝቃዜ ሁኔታ ከባለፉት ሁለት የበጋ ወራቶች በተለየ እየጨመረ የሚሄድ ሲሆን በሌሎች መካከለኛ እና ዝቅተኛ ቦታዎች ላይ በሰዎች ጤንነት ላይ አሉታዎ ተፅዕኖ የማይኖር ሲሆን በሌላ በኩል ለእንሰሳት ምርትና ምርታማነት እንዲሁም ጤንነት ምንም አይነት አሉታዊ ተፅዕኖ እንደማይኖር ይጠበቃል ያሳያሉ።